አጭር ቃለ ምልልስ ከእትዬ መሰረት ጽጌ እና ጋሽ እንዳልካቸው ኪዳነመርቅ

ጎሬ በሚገኘው ቤተል መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በዝማሬ ከረጅም ዘመናት አገልግለዋል። እንደነ "የአዲስ ኪዳን በግ፣ የጽዮን ግርማዊ፣ በደመና ይመለሳል" ያሉት ዝማሬዎቻቸው በጊዜው ከነበራቸው የልጅነት አዕምሮ የመጣ የሚይመስሉ ሲሆኑ ከወንጌል መስፋፋትም ጌታ በዘመናት መካከል የተጠቀማበቸው ናቸው። ከምድራችን የዝማሬ አድገት በደስታ ብዙ ከለፉ ቅዱሳን መካከል እነዚህ ባለትዳር እንዶቹ ናቸው። እግዚአብሔር እድሉን ሰጥቶን ስለዝማሬ አገልግሎት ያላቸውን ሃሳብ ጠይቀናቸው እንዲህ ብለውናል

መዝሙር መጻፍ እንደት ጀመራችሁ?

እትዬ መሰረት ፦ ከእኛ ቀደም በዚያን ጊዜ ሚንም መዝሙር ሲጽፍ አይተን ስለሚናውቅ መዝሙር መጻፍ ከእኛ አዲስ ነገር ነበር። አዲስ አበባ ያሉ መዘምራን መዝሙር እንደሚጽፉ ብንሰማም እኛ ግን ሞክረን አናውቅም ነበር። አንድ ጊዜ ኮንፍራንስ በቤተ ክርስቲያናችን ተዘጋጅቶ ዝማሬ እንድናቀርብ ስንጠየቅ ከእንዲት እህት ጋር ጌታ እንዲረዳን መፀለይ ጀመርን። ጌታም ፀሎታችንን ሰማና እንደሚያቋርጥ ጅረት ዝማሬ ከውስጣችን ይመጣ ጀመረ። ነገር ግን ልምድ ስላልነበረን ፍርሃቱም ስለነበር ከመጽሃፍ ቅዱስ ሃሳብ፣ ሰባኪዎች ከሚሰብኩት፣ መይም በቃሉ ካነበብነው ብዙ መራቅ እንፈልግም ነበር፤ ከስህተት ለመጠበቅ ስንል።

የአገልግሎት ዘመናችሁ ምን ይመስል ነበር?

እትዬ መሰረት ፦ አንድ ጊዜ የነበርኩበት ኳየር ወደ አዲስ አበባ ከአገልግሎት ተጠራና አዲስ አበባ ከሚገኙ ኳየሮች ጋር አብረን እንደምንዘምር ስንሰማ እጅግ ፈርተን ነበር። ምክንያቱም ወጣ ብሉን አገልግሉን አናውቅም፣ ድምፅ አወጣጣችንም የተቀነባበረ አልነበረም፣መዚቃ መሳሪያ አጨዋወታችንም እምብዛም ነበረ፣ የአዲስ አበባም መዘምራን ብዙ ልምዱ ከነበራቸው ነበሩ። ነገር ግን ከአገልግሎት በኃላ ብዙዎች እጅግ እንደተባረኩ ሲነግሩን በጣም ተበረታታን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጌታ ልባችንን በድፍረት ሞላው አዳዲስ ቃላትም ይፈልቁ ጀመር።

መዝሙሮቻችሁ ትልቅ ተፅዕኖ ኪኖራቸው የቻለው ለምን ይመስላችኋል?

ጋሽ እንዳልካቸው ፦ መዝሙሮቹ እንዲህ ኃይለኛ ሆነው ኪቆዩ የቻሉት በዚያን ጊዜ ታላቅ የመንፈሳዊ መነቃቃት በምድሪቷ መጥቶ ስለነበርና መዝሙሮቹም የዚያ አሳት ውጤት ስለሆኑ ይመስለኛል። ወገኖች ካይ ቃሉን የሚንበብ አእምሮና ልባቸውን በጌታ ቃል የመመሩካት በፀሎትም የመትጋት ጥማት መርዶ ነበር። በጥቅሉ መዝሙሮቹ ከጌታ ጋር የመቀየት ውጤት ናቸው።

እትዬ መሰረት ፦ የተማርነው የመዝመር አጻጻፍ ባይኖርም የፀሎት ሰዎች ግን እንደነበርን እኔም አስታውሳለሁ። በምድራችን ብዙ የጌታ ስራ እንዲሰራ ቤተ ክርስቲያናችንም እንድታድግ ብርቱ የፀሎት ጉልበት በአገልጋዬች ካይ መርዶ ነበር። ጌታም በምክር በጸሎት በምልጃና ከጊዜው በሆኑ መልእክቶች ይሞካን ነበር።

ለሚቀጥለው ትውልድ ምን የምታስተላልፉት መልዕክት አላችሁ?

እትዬ መሰረት፦ ይህ ትውልድ ሰው በራሱ እንደሚይበረታ ተገንዝቦ ከሕዝቡ የሚጠቅም ዘላቂ ምክር መደሚመክር ጌታ በፀሎትና በቃሉ መጠጋት ያስፈልገዋል እላለሁ። በእእምሮ ቃላትን መግጠም መልካም ቢሆንም በጌታ መንፈስ ውስጥ ሆኖ የእርሱን ሃሳብ ማስተላለፍ ደግሞ ይበልጥ የተሻለ ነው እላለሁ።

ጋሽ እንዳልካቸው ፦ ይህ ትውልድ ጌታን ማያመልክ የሚወድ እንደሆነ አውቃለሁ ከዚህ በበለጠ የጌታ ሃይል እንዲገለጥበት ወደ ቃሉ ጥልቀት እንዲሄድ እኔም እላለሁ። እግዚአብሔርን ስንፈልገው በቅድስናና በፅድቅ መኖር እንሻለን እርሱም በእኛ ለመገለጥ ይመቸዋል።